በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በስታስቲክስ መረጃ

አገራችን ኢትዮጵያ 2 ሺ /2000/ በዓልን ለማክበር የተለያዩ ዝግጅቶች በየዘርፉ እያካሔዳች ነው።

2000ና ጌታችን መድኃኒታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ**፣ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል **ማርያም** ተወልዶ እኛን ከኃጢአትና ከሲኦል ያወጣበት ጊዜ አንድና አንድ ናቸው። ለዚህም ነው ዕሥራ ምእት በመላው የክርስትና ዓለም እንዲሆን የተወሰነው። የክርስቶስ ልደትና የክርስትና ወደ ሀገራችን መግባት እጅግ ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው። ቀጥሎም በሰባተኛው ምእት ዓመት ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት ወደ አገራችን እንደገባ የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ።

ይሁን እንጂ በተለያየ **ጊዜና** በአንዳንድ ቦታ የነዚህ ሃይማኖት እማኞች ቦታ የነዚህ ሃይማኖት አማኞች ስርጭት እጅግ ጉልቶና ገዝፎ በተዛባ መለኩ ሲነገርና ሲዘከር ይታያል። በመሆኑም በየእምነቶቹ ምእመናን አእምሮ የተሳሳተ አመለካከተ እንዲኖር አድርጓል። ከርእሱ ለመረዳት እንደሚቻለው የዘህ ጽሑፍ ዓላማ የእነዚህን ሃይማኖቶች ስርጭተ በእውነተኛ መረጃ ላይ በመመርኮዝ በእስታቲስቲክስ አስደግፎ ለማቅረብ ነው።

ይህ ጽሑፈ የተዘጋጀበት አጋጣሚ አገራችን ኢትዮጵያ ለሦስተኛ ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በግንቦት ወር 1999 ለማካሔድ ቅድመ ዝግጅቶችን እያገባደደች ባለችበት ጊዜ በመሆኑ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ አኳያ ስለ ሕዝብ ቆጠራ አንዳንድ ታሪካዊ ጭብጦችን ማቅረብ ተገቢ ነው። የሕዝብ ቆጠራ በባቢሎን በ3,800 ከክርስቶስ ልደት በፊት፤ በቻይና ደግሞ በ3,600 ከ**ክርስቶስ** ልደት በፊት እንደተካሔደ የታሪክ ተመራማሪዎች ደርሰውበታል። ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፋችን ይሆን ዘንድ በታላቁ መጽሐፍ - በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት የሕዝብ ቆጠራ አጋጣሚዎችን መጥቀስ ይበቃል። በተለያዩ ቦታዎች እንደተጠቀሰው እስከ ጌታችን መድኃኒታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ** ልደት ጊዜ ድረስ ከስድስት ያላነሱ የሕዝብ ቆጠራዎች ተካሒደዋል።

- በመጀመሪያው ቆጠራ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ በባርነት ይኖርበት ከነበረው ከግብጽ ምድር **በእግዚአብሔር** ትእዛዝ ይዞ በወጣ በአራተኛው ወር በሲና በረሃ በድንኳን ሠፍረው ሳለ የተደረገው ነው። በዚህ ቆጠራ የተመዘገቡት ሃያ ዓመት የሞላቸውና ከዚያም በላየ የሆኑት 603,550 ወንዶች ነበሩ። /አሪት ዘፀአት 38፣26/

- በሁለተኛው የሕዝብ ቆጠራ የተካሔደው የእስራኤል ሕዝብ ከግብስ በወጡ በሁለተኛው ዓመት ሁለተኛው ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን በሲና በረሃ ሳሉ **እግዚአብሔር** እራሱ በሚመለክበት ድንኳን ውስጥ ሙሴን «አንተና አሮን በየነገዱና በየቤተሰቡ ከፍላችሁ ያእስራኤልን ሕዝብ ቁጠሩ ዕድሜአቸው ሃያ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሆኖ በወታደርነት ማገልገል የሚችሉትን ወንዶች ሁሉ በየክፍለ ጦራቸው መዝግቡ» ሲል አነጋገረው። /ዘኁልቁ1፡1/ በዚህ ቆጠራም የእስራኤላውያን ወንዶች ጠቅላላ ቁጥር ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ነበር። /ዘኁልቁ 26፣5/

- ሦስተኛው የሕዝብ ቆጠራ በዳዊት ዘመን የተደረገው ሲሆን **እግዚአብሔር** በእስራኤል ሕዝብ ላየ ስለተቆጣም በዳዊት አማካኝነት መክራ ሊሰጣቸው በማለት ዳዊትን እንዲህ አለው። ሄደህ የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ ቁጥር አለው። ዳዊትም ኢዮአብን ጠርቶ ከአገራቱ ዳር እስከ ዳር ማለትም ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ወደሉት የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ሔደህ ሕዝቡን ቁጠር። ምን ያህል ሕዝብ እንዳለ ማወቅ እፈልጋለሁ ሲል አዘዘው። /2ኛ መጽ.ሣሙ. 24፣1-3/ ቆጠራውን ለማካሄድ ዘጠኝ ወር ከሃያ ቀን ከፈጁ በኋላ በእስራኤል ስምንት መቶ ሺህ በውትድርና ለማገልገል ብቃት ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን ለንጉስ ደዊት አሳውቁ። /2ኛ መጽ.ሣሙ. 24፣9/

- አራተኛው ቆጠራ ንጉስ ሰሎሞን ያደረገው ሲሆን ለእስራኤል ምድር የሚኖሩትን የውጭ አገር ሰዎተ ቆጠረ። በቆጠራው ውጤትም አንድ መቶ ኀምሣ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ የውጭ አገር ሰዎች መኖራቸው ተረጋገጠ። /2ኛ መጽ.ዜና መዋዕል 2፣17/

አምስተኛው ቆጠራ በፋርስ ንጉስ በቂሮስ የተደረገው ሲሆን ይህም የተካሔደው ወደ ሀገራቸው የተመለሱ እስራኤላውያን ስደተኞችን ዝርዝር ለማወቅ ሲባለ ነበር። በዚህ ቆጠራ ከስደት የተመለሱት ሰዎች ጠቅላላ ብዛት 42ሺ360 ነበር። /ዕዝ.2፣64/ የእነዚህም ወንዶችና ሰቶች መዘምራን ድምር 200 ነበር።

ስድስተኛው ቆጠራ **ኢየሱስ ክርስቶስ** ከተወለደ በኋላ የሮማው ቄሳር አውግስጦስ

በሮማውያን ግዛት ያሉ ሰዎች ሁሉ በሕዝብ ቆጠራ እንዲመዘገቡ ያዘዘበት ነው። /ሉቃስ 2/ በዚህም ከ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ልደት በፊት በተደረገ የሕዝብ ቆጠራ እያንዳንዱ ሰው ስሙን ለማስመዝገብ ወደ ትውልድ አገሩ ይሔድ ነበር። ዮሴፍም በገሊላ አውራጃ ከምትገኘው ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ሄደ። ይህንንም ያደረገው እርሱ በትውልዱ የዳዊት ዘር ስለነበረ ነው። ለቆጠራው ወደ አገሩ

የሔደው በመንፈስ ቅዱስ ግብር ፀንሳ ከነበረችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ነበር። በዚያም የበኩር ልጇን **መድኃኔ ዓለምን** ወለደች። በመታቀፊያ ጨርቅ ጠቀለለችው። በእንግዶች ማደሪያ ሥፍራ ስላላገኙ በበረት በከብቶች መመገቢያ ግርግም ውስጥ አስተኛችው። /ሉቃ.2፣4-6/

በዚህ ዓይነት በተለያየ ጊዜ ለተለያየ ዓላማ በተለያየ ጊዜ ለተለያየ ዓላማ ሲካሔድ የነበረው የሕዝብ ቆጠራ በጊዜ ብዛት በነገድ፣ ወንድና ሴት ቁጥር ብቻ ከመወሰን አልፎ ዕድሜን፣ ሃይማኖትን፣ የኃብቻ፣ የትምህርት፣ የሥራ፣ የወሊድ ሁኔታን፣ የቤቶች ሁኔታን ... ወዘተ የመሳሰሉት መረጃዎችን ጨምሮ በዘመናዊ መልኩ የተካሔደው በአሜሪካ እ.ኤ.አ በ1790፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ በ1801 ነበር። አገራችን ኢትዮጵያም የዚህን ዓይነቱን ቆጠራ የመጀመሪያውን በግንቦት ወር 1976ዓ.ም.፣ ሁለተኛውን ደግሞ በጥምቀት ወር 1987 አካሒዳለች።

አገራችን ሦስተኛውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስታካሒድ ቤተክርስቲያን ሊቃውንቶቿን፣ መምህራኖቿን በማስተባበርና በሥሯ ያሉትን አዕላፍ ምእመናን በማስተማር የሕዝብ ቆጠራው የታለመለትን ግብ እንዲመታ የበኩሏን ጥረት እንድታደርግ **እግዚአብሔር** ይርዳን፣ አሜን።

በጽሑፍ ትንተና ጸሓፊው መሠረት ያደረገው አገራችን ከዚህ ቀደም 1976ዓ.ም. እና 1987ዓ.ም. በአካሔዳቻቸው ሁለት የሕዝብና የቤት ቆጠራዎች የተገኙ መረጃዎችን ነው። የሕዝብና የቤት ቆጠራ መረጃ የተመረጠበት ዐቢይ ምክንያት የዚህ አይነቱ የመረጃ አሰባሰብ አገር አቀፍና በናሙና ሳይሆን ከቤት ወደ ቤት እየተሄደ ያለአንዳች የጸታ፣ የዕድሜ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ የቀለምና የፖለቲካ ድርጅት ወዘተ ልዩነት ከሁለም ክልሎችና ከሁሉም የሀገሪቱ ዜጐች በእኩልነት ላይ በተመሠረተ መርሕ የተሰበሰበ በመሆኑ ነው። ስለሆነም በጽሑፉ ምእመናኑ ትክክለኛው ግንዛቤ እንዲኖራቸው የየሃይማኖቶቹን ተከታዮች በብሔረሰብ፣ በክልል፣ በዞን፣ በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ ለያይቶ ለማቅረብ ተሞክሯል።

yx!T×ùÃ ?ZB B²T bXMnT SR+T bKLLÂ bøN

አገራችን ለመሪጀመሪያ ጊዜ ባካሔደችው የሕዝብና የቤት ቆጠራ /በ1976ዓ.ም./ መሠረት በወቅቱ ከአጠቃላይ ሕዝቧ መካከል 60.5 ከመቶ የሚሆኑት የክርስትና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ 24 ከመቶ የአስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ነበሩ። 5.8 ከመቶ የሚሆኑት ባህላዊ አምልኮት ማለትም እንደ ዛፎች፣ ወንዞች፣ ተራራዎች፣ በመሳሰሉት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ክስተቶች አምላኪዎች ነበሩ። በክርስትናና በእስልምና እምነት ላየ ስናተኩር በ1976ዓ.ም. በከተማ ይኖሩ ከነበሩ ሕዝቦች 81.4 ከመቶ ክርስቲያኖች፣ 17.1 ከመቶ ደግሞ እስላሞች እንደነበሩ ያሳያል። በገጠር የመቶኛው ቁጥር ለክርስቲያን አማኞች ወደ 57 ከመቶ ዝቅ ሲል ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ ወደ 35 ከመቶ ከፍ ይል እንደነበር መረጃዎች ጠቁመዋል።

ይህ በተመሳሳይ አካሔድ ከአሥራ አንድ ዓመት በኋላ በጥቅምት 1987 በተካሔደው ቆጠራ ከጠቅላላ የአገራችን ሕዝቦች 62 ከመቶው ክርስቲያን 32.8 ከመቶው እስላም መሆናቸው ታይቷል። የከተማና የገጠር ስብጥሩን ስናይ እንደ 1976 ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በከተማ 75 ከመቶ ሲሆኑ በገጠር 60 ከመቶ ነበሩ። በአንጻሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች 24 ከመቶ በከተማ 34 ከመቶ በገጠር ነበር። ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው ከሁለቱም የቆጠራ ውጤቶች የክርስትና እምነት ተከታዮች ቁጥር በእጅጉ የበለጠ መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ 1987 ሕዝብና ቤት ቆጠራን ብቻ ብናይ በአጠቃላይ መልኩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ከእስልምና ሃይማኖት በእጥፍ እንደሚበልጡ ነው።

ሠንጠረዥ ሀ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በሃይማኖት ስብጥር፣ 1976 እና 1987

ሃይማኖት	1976			1987		
ድምር	ከተማ	ገጠር	ድምር	ከተማ	ገጠር	
ክርስቲያን	60.48	81.44	57.42	61.70	75.20	59.40
ሙስሊም	23.90	17.71	35.12	32.80	24.00	34.20
ባህላዊ	5.79	0.31	6.59	4.60	0.20	5.30
ሌሎች	0.65	0.27	0.71	0.90	0.40	1.00

ከተሜውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ የወሰድን እንደሆነ ደግሞ የስታቲስትክስ ገጽታው ይቀየራል። ማለትመ የክርስትና እምነት ተከታዮች በሦስት እጥፍ ይበልጣል /75 ከመቶና 24 ከመቶው/ በሠንጠረዡ የተገለጸውን ይመልከቱ። ከዚህ መረጃ የምንረደው የስርጭቱ መጠን ይህ ነው የሚባልና ስታትስትካዊ ፋይዳ ያለው ለውጠ ያላመጣ መሆኑን ነው።

ከላይ የተገለጸውን አኃዝ እንዳለ በመቀበል በሁሉም ክልሎች ይኸው ገጸታ ይንፀባረቃል ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ስሕተት ላይ ስለሚጥል የየሃይማኖቶቹን ተከታዮች ስብጥር በክልሎች ነጣጥሎ ማየት ተገቢ

ይሆናል። በዚህም መሠረት ከሠንጠረዥ «ለ» ለማየት እንደሚቻለው በየሃይማኖቶቹ ረገድ በየክልሎቹ የስርጭቱ መጠን የተለያየና ልዩነቱ ጐልቶ የሚታይ መሆኑን ነው። ለአብነት ያህል የክርስትና እምነት ተከታዮች በትግራይ 95.8 ከመቶ ሲሆኑ በአፋር 4.3 ከመቶ፣ በሱማሌ ክልል ደግሞ 1.1 ከመቶ ናቸው። በተቃራኒው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በትግራይ 4.1 ከመቶ ሲሆኑ በአፋር 95.7 ከመቶ፣ በሱማሌ 98.8 ከመቶ ናቸው። ከመረጃው በመነሳት በአማራ 81.5 ከመቶ፣ በአዲስ አበባ 86.7 ከመቶ፣ በጋምቤላ 71.3 ከመቶ፣ በደቡብ ሕዝቦች 65.4 ከመቶ እና በኦሮሚያ 50.4 ከመቶ የክርስትና ተከታዮች ናቸው።

ከቆጠራው መረጃ ለመረዳት የሚቻለው በነዚህ አራት ክልሎች ማለትም በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ሕዝቦች ክልሎች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት ከአገራችን ሕዝቦች ከ86 ከመቶ በላየ የሚሆነው መሆኑን ነው። የሃይማኖቶቹ ተከታዮች ስብጥር በቤኒሻንጉል የተለየ መቶኛ አኃዝ ያሳያል። ይኸውም ከክልሉ ሕዝብ 41 ከመቶው ክርስቲያን 44 ከመቶው ደግሞ ሙስሊም ነው። በሌላ በኩል በአፋር፣ በሱማሌ በድሬዳዋና በሐረር ከሚኖሩት ሕዝቦች በአብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ናቸው።

ሠንጠረዥ ለ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በሃይማኖት ስብጥርና በክልል

	ሃይማኖት			
ክልል	ክርስቲያን	እስላም	ባህላዊ አምልኮት	ሌሎች
ትግራይ	95.80	4.10	0.00	0.00
አፋር	4.30	95.70	0.00	0.00
አማራ	81.50	18.40	0.00	0.00
ኦሮሚያ	50.44	44.27	4.21	0.98
ሱማሌ	1.10	98.80	0.10	0.00
ቤኒሻንጉል	41.10	44.10	13.10	1.50
ደ/ብ/ብ/ሕዝቦች	65.40	16.70	15.40	2.40
ጋምቤላ	71.30	5.10	10.30	12.70
ሐረሪ	39.50	60.20	0.00	0.10
አዲስ አበባ	86.70	12.70	0.60	0.00
ድሬዳዋ	36.70	63.10	0.00	0.10
ጠቅላላ	61.70	32.80	4.60	0.9

ምንጭ፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1987 የክልሎቹ የትንተና ሪፖርተሮች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ 2000 ዐውደ ጥናት ዝግጅት ልዩ እትም ሚያዝያ 1999 ዓ.ም አዲስ አበባ

መስቀሉ ለእግዚአብሔር